# ሰው እኮ ወዶ አይስቅም! ከመይ ከመይ ወዲ ደደቢት?

ከአያልነሽ

ዕድሜ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዓለም እንዴት አደረች ብዬ ውሎና አዳሯን ለመጎብኘት ብቅ ማለቴ አልቀረም። የእኔይቱ እገር ኢትዮጵያም እዚሁ ዓለም ውስጥ ነውና የምትገኘው ነጋ ጠባ ዓለምን ስዳሥሥ ይበልጥ ትኩረቴን ያደረኩት ደግሞ እዚቺው በጣር ላይ በምትገኘው ኢትዮጵያ አገራችን ላይ ነው። ይህ መቼም የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የዕለት ተዕለት ሥራና ተግባር ነው ብል ማጋነን አይሆንም። ኢትዮጵያችን አሁን የምትገኝበትና የገጠማት ባላንጣ በታሪኳ ያላየችውና ያልገጠማት ነውና ጭንቋ፣ ጣሯና ጩኸቷ ቢያባዝነንና እንቅልፍ ቢነሳን ግዴታ ነውና ልንሸሸው አንችልም። አገር ናትና አገር ሆና በመቀጠሏም አሁን በመዳፉ ሥር አድርጎ የሚያስጨንቃት ባላንጣ ባጋጣሚ እጣ ፈንታዋ ሆኖ እየናጣት ይገኛል።

ይህች በክፉ አገዛዝ ሥር እየማቀቀችና ሕዝቧም በክፉ አገዛዝ ሥር ታስሮባት ''የአገር ያለህ'' እያለች በመጨህ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ፣ ድራሿንም ለማጥፋት ይሁነኝ ብሎ ሌት ተቀን እየሠራ የሚገኘው ወያኔ ዛሬ ደግሞ ታሪክ ደርቶ አቅርቧል።
ትናንትና የአክሱም ሐውልት ለአማራው፣ ለኦሮሞው፣ ለወላይታው፣ ለጉራጌው፣ ለጋምቤላው፣ ለአፋር፣ ለኮንሶው፣ ለሀድያው፣ ለዶርዜው፣ ለጉምዙ፣ ለሻንቅላው፣ ለቅማንቱ፣ ወዘተ.... ምኑ ነው? እያለ አረፋ ሲደፍቅ እንዳልነበረ፣ ዛሬ ደግሞ በአለቀ ሠዓት ''ልጅ ለእናት ምጥ አስተማረች! ዘረ ቢሶች በኢትዮጵያዊነት ሲነግዱ'' ብሎ ዓይጋ



ጀግኖች አባቶቻችን

ይሄን ከላይ የአስቀምትኩትን ፎቶ ሲለጥፍ አይቼ እጅግ አዘንኩ። ሃዘኔ በወያኔ ላይ አይደለም። ወያኔማ ሊያጠፋት የተነሳ ጠላቷ ነውና አይደንቅም። ኃዘኔ ወያኔን በሚከተሉና በሚያጅቡት እንጅ።

ኢትዮጵያ ሆይ! አንችው ተቸግረሽ ተከፍተሽ፣ ጎንሽ ስይደነድን ይበልጥም ተወግተሽ፣ በአንች መከፋት ጥቂቶች አምሮባቸው፣ በአንች መጎዳት እብሪተኞች ፈንድቀው፣ አንች በመኖርሽ መኖራቸውን ዘንግተው፣ ያልተነካ እምቅ ሀብትሽን ጥቂቶች ተቆጣጥረው እየተምነሸነሹ ባሉበት ሁኔታ ደሃ ናት እያሉ ሲለምኑብሽ፣ አንች ተጎድተሽ ተቀማጥለው ያደጉብሽ፣ አንችነትሽን ጠልተው ታሪክሽን አጉድፈው፣ ሀብትሽንም ዘርፈው ከጥጋብ በላይ ሆነው ና ውረድ እግዚአብሔር የሚሉ ዘመነኞች ፣ ይሄ ሁሉ ጥጋብ አንሷቸው በታሪክሽ በሚዘባበቱ ወንበዴዎች ሥር መውደቅሽ የምፀት ምፀት ነው።

አርዕስቴን ''ሰው እኮ ወዶ አይስቅም'' ያልኩበት ወያኔ ሁሉም ነገሩ ምን ያህል ያለቀበት መሆኑን ስመለከት ሳልወድ በግድ ስለሚያስቀኝ ነው። እንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ሲያጋጥም ነው መሰለኝ ''ጥርስ እኮ ወዶ አይስቅም'' የሚሉት። እንዲህ ነው፤ ለመጻፍ

ያነሳሳኝ ይህ ከላይ የተለጠፈው ጉደኛው የዓይጋ ፎቶ ነው። ዘይገርም ሻሽመኔ! ነው መስል የሚባለው። የወያኔ ነገር ሁሌም ያስገርመኛል። የሚያስገርመው የሀገር ስርቆቱና የታሪክ ዝርፊያው ለእኔ አዲስ ሆኖብኝ ሳይሆን ብጻይ ዓይጋ "ጀግኖች አባቶቻችን" ብሎ በለጠፈው ላይ የተጋዳላይ ኃያሎም አርዓያ ፎቶንም ከእነኝህ ቀደምት የኢትዮጵያ ባለታሪኮች ጋር አብሮ ማቆሙ ቢደንቀኝ ነው።

ይቅርታ! ሙት ወቃሽ አያድርገኝና በወያኔ እጅ ስለተቀጠፈው ኃያሎም አርዓያ በወያኔ ውስጥ ስለነበረው ሚናና ስለ አገዳደሉም ቢሆን ብዙ ሊፃፍበት የሚያበቃ ሚስጥራዊ ሰነድ በብዙዎቻችን እጅ ውስጥ ስለሚገኝ መጻፍ በሚያስፈልግበት ጊዜ ወቅት ጠብቆ መጻፉ አይቀርም። የሆኖ ሆኖ ግን ወያኔ ራሱ ያጠፋውንና የገደለውን በየትኛው የወያኔ ስሌት ይሆን ከእነኝህ ኢትዮጵያዊ ባለታሪኮች ጋር ኃያሎም አርዓያን አብሮ ለጥፎ ያቀረበው? ብሎ መጠየቅ ግን አግባብነት አለው። ወያኔ በህይወት የሌሉ (በሞት ያለፉ)፣ እሱ ባልነበረበትና ባልተፈጠረበት ጊዜ እንኳ ሕይወታቸው ያለፈውን ሁሉ በሌሉበት "ፍርድ ቤት" የሚያቆምና "የሞት ፍርድ" ፈርጃለሁ የሚል ጉግማንጉግ ነውና መጠየቄ ከወያኔ መልስ ይገኝበታል ብዬ ሳይሆን ኢትዮጵያ በምን ዓይነት ሰዎች እጅ ውስጥ እንደወደቀች አሁንም ለማመላከት አስቤ ነው። ይህ ከደደቢት የፈለሰ የወያኔ ቡድን ራሱ የገደለውን ኃያሎም አርዓያን ለምን እንዳስገደለውና እንደገደለው ደፍሮ ሊናገር ባልቻለበት ሁኔታ፣ ተመልሶ የገደለውን ሬሣ (ሬሣ አይናገርምና) በሬሣው ላይ ዛሬም ሊነግድ ሲነሳ ይብላኝ "ወርቅ ዘር" ላላቸው እንጅ እኛማ ለእነ ወያኔ እጅግ ሩቆች እንደሆንንና እንደነበርን ያወቅነው ገና ከደደቢት ዋሻው ዳዴ ሲል ነበር። ይህ ሰው መሳይ አራዊት የሆነ ነገር፣ የሚያደርገው ድርጊት ሁሉ ሰብዓዊ ለሆነ ፍጡር የሚሰቀጥጥ ቢሆንም 'ጥሎብን' በእኛም ላይ ደርሶ በአደባባይ በኩራት የሚያደርገው ተግባሩ ነውና እንደብቀው ብንል የማይቻል ገመና ነው። ይብላኝ ለተከታዮችና ለአድናቂዎቹ! አሳዛኝ ተፈጥሮ።

የገደለውን ከመቃብር አውጥቶ ዳግም ለሚገድል፣ የቀበረውን ሬሣ ከጉድጓድ አውጥቶ "ፍርድ ቤት አቆምኩ" ብሎ ሬሣን እንደገና ለሚከሥና ለሚሞግት፣ ለእንዲህ ዓይነት አውሬ ተከታይና አዳናቂዎች ማግኘቱ ይበልጥ ሰቅጣጭና ሰው የተባለውን ፍጡር "ሰውነት" ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው። ወያኔ ምንም ቢሆን ምን ቂመኛና በበቀል የታጀለ ቡድን ነውና ባህሪውን በፈለገው ያህል ወርቅ ሊለብደው ቢሞክር በምንም ተዓምር ይህን ተፈጥሮውን መሸፈን አይችልም። ቂመኛና የበቀል ሰው ነው ስንል የሌለውን ባህሪ ሳይሆን ተኮትኩቶ ያደገበትና የኖረበት አንጡራ ሃብቱና ፍጥረቱ በመሆኑ ነው። አሁን ሰሞኑን "ጀግኖች አባቶቻችን" ብሎ ዓይጋ የለጠፈው ፎቶ ከዚህ ቀደም ሲያጣጥላቸውና ታሪካቸውን ጥላሸት ሲቀባ የኖረው ወያኔ (እርግጥ ተጨንቆ ቢሆንም) የ"ወርቁን ዘር"ኃያሎም አርዓያን ከእነኝህ "ኋላቀር ቀደምት ኢትዮጵያኖች" ጋር ጨምሮ ማውጣቱ አጀብ የሚያሰኝ ነው።

"<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሣ</u>" ተብሎ የተገጠመለትና ለታላቋ ኢትዮጵያ ክብር ሲል በነጭ እጅ መውደቅን እንደ ውርደት ቆጥሮ፣ ሽጉጡን ጠጥቶ ጀግንነቱን ያስመሰከረና ራሳቸው ነጮቹ ጀግንነቱ እስኪደንቃቸው ድረስ የናኙለት ባለታሪኩ (አጼ ተዎድሮስ) ጋር በየትኛው የወያኔ ስሌትና ቀመር ይሆን ኃያሎም አርዓያን አብሮ ከእነኝህ ጋር ሊያቆም የደከመው? ይሄንን ጥያቄ እንኳን እኔ ወያኔም ራሱ መልስ የለውም። አሁን በዘርና በጎሳ ሸንሽኖ ትንንሽ "ክልል" ሊሰራ የሚሞክረው ወያኔ እነ ቴዎድሮስ የሠሯትን ኢትዮጵያን ሲያውግዝና ሲረግም ነው የኖረው። ዛሬ ወያኔዎች የሚዘርፏትና ባለ ሃብት ያደረገቻቸው

ኢትዮጵያን ያገኟት እነኝህ ቀደምት የኢትዮጵያ ባለታሪኮች በሰሩት ጅብዱና በከፈሉት መስዋዕትነት ነው። የእነኝህን ባለታሪኮች ገድልና ጀግንነታቸውን ሳይቀር ከአፈር ጋ ሲደባልቅ የኖረው ወያኔ፣ መቃብራቸውን ሁሉ እያንኳኳ፤ ይህን አረጉ ያንን ፈጁ እያለ አጥንታቸውን ሲሰብርና ሲሰባብር የኖረ ነው። ዛሬ ደግሞ አባ በዝብዝ ካሳ (አፄ ዮሐንስ) አንገታቸውን የተሰየፉበትና ያስቀረጡበትን መተማ አሳልፎ ለሱዳን በስጦታ በሰጠበትና አገር ቆርሶ እየሸጠ ባለበት ሁኔታ በምንም መልኩ የማይገናኝና የማይገጣጠመ ነገር ደርቶ አይኑን በጨው አጥቦ ታሪክ ብሎ ይዞ ቀርቧል። አባ ታጠቅ ካሣ (አፄ ቴዎድሮስ) ያኔ በእነሱ ጊዜ በመሣፍንታዊ ሥርዓት ውስጥ የነበረችን ሀገር ከዚያ አውጥቶ ትልቂቱን ኢትዮጵያ በማቆመ ይህችን ኢትዮጵያ የተባለች ሐገር ያስረከበንን አንበሣ፣ ይህንን የሱን ዓላማ ተፃሮ ለተበጣጣሰች ትንንሽ ''ክልል'' የተጋደለውን የኃያሎም አርዓያን ፎቶ አምጥቶ ከእነኝህ የኢትዮጵያ ባለውለታዎች ጋር አብሮ መለጠፉ በየትኛው የወያኔ ሚዛን ይሆን የተለካው? ኃያሎም በወያኔ ተሰልፎ (ወያኔ እስኪገድለው ድረስ) የታገለው ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለትግራይ ''ነፃነት'' ነው። ታዲያ የዚህ ታሪክ ባለቤት የሆነው ኃያሎምስ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ከእነ አፄ ቴዎድሮስ ጋር የተለጠፈውን ይሄንን የእሱን ምስል ቢያይ ከእነርሱ ጋር የእርሱ ፎቶ መለጠፉን ይመኘውና ይወደው ነበር ይሆን? አሁንስ የእሱን መሰመር እየቀጠልኩ ነው የሚለውና የኃያሎምን ሕይወት ያጠፋው ድርጅቱ ወያኔ፣ እነኝህን ቀደምት የኢትዮጵያ ባለታሪኮች ከተኙበት እየቀሰቀሰ ምን ሲላቸው ነበር? ለምን ያህል ጊዜስ ሲረግማቸው ኖረ? ዛሬስ የኃያሎምን ምስል ከእነኝህ ቀደምት የኢትዮጵያ ባለታሪኮች ጎን ሲያስቀመጥ የእምዬ ምንሊክን ምስል/ፎቶ በኃያሎም አርዓያ መተካቱ ለምን ይሆን? እግዚኦ! ምን ዓይነት ሳጥናዔል ነው የመጣብን ወገኖቼ?!

ወያኔን አምናችሁ ለምትከተሉት የትግራይ ልጆች ሆይ! እባካችሁ! ጩኼቴን አዳምጡኝ። እግዚኦ ብዬ ብሶቴን የማሰማችሁ ኃያሎምን አሁን ዛሬ ለእናንተ ''ዓርበኛችሁ'' ሊያደርግው የሚኳትነው ወያኔ ትናትና እናንተም እያያችሁ፣ እየሰማችሁ በጠራራ ፀሐይ ላይ ያስገደለውን ኃያሎም አርዓያን ነው። ይህንን አታውቁምን? ኃያሎምማ ይህንን ጭካኔ አሁን አያይም፣ አይሰማምም። ሌላው ቢቀር ከሰው ነው የተፈጠረውና የእሱን ዘመዶችና ወገኖቹን፥ ቋሚዎቹን ነው ወያኔ ዳግመኛ እየገደለ ያለው እላችኋለሁ። እባካችሁ! መንገዳችሁን መርምሩት? ዓይናችሁንም ገለጥ አድርጋችሁ ተመለከቱ! ጆሮአችሁንም ከፍታችሁ በደንብ አዳምጡ እባካችሁ!

እንዲያው ለነገሩ ''ገዳዩ ባሏ ሟቹ ወንድሟ'' የሚባል ነገር ሰምታችኋልን? ''የአማራ'' ተረት መሰሏችሁ እንዳትናንቁት አደራችሁን። በወያኔ የምናየው ድርጊት ይሄው ነው፥ አዝናለሁ። ወያኔ ኃያሎምን ገድሎ ሬሣውን በአበባ ጉንጉን ያሽቆጠቁጣል፤ የኃያሎምን ነፍስ አጥፍቶ የአበባ ጉንጉኑን ውኃ ያጠጣል - አሳዛኝ፣ ዘግናኝና ሰቅጣጭ ታሪክና ጉዞ! እንዲህ እንዲህ ዓይነት የማይገናኝን ነገር ገጣጥሞ በመደረት ''ቆርጠ ቀጥል'' የሚል ስም የተሰጠው ወያኔ፣ ይህንን ቃል እንደ ጌጥ ቆጥሮትና ልብስ አድርጎት እንደ ሸማ ተከናንቦት ሲዞርና ሲኖር ድፍን 33 ዓመት አስቆጥሯል። በኢትዮጵያዊነት ሥነ ምግባር ላደገና ለተቀረጸ ሰው ደግሞ ይህ ''ቆርጠ ቀጥል'' የሚል ቃልና አገላለጽ አስተዳደግንና አሳዳጊንም የሚዳሥሥና የሚነካ በመሆኑ ለብዙዎቻችን ለሥነ ቃሉ ያለን ግምት አሉታዊ የምንሸሸው ነው። ለወያኔና መሰሎቹ ግን ጌጥና ልብስ መሆኑ ነው። እንዲህ፥ እንዲህ ዓይነት ሥነ ልቡና ያላቸው ሰዎች በማንኛውም ህ/ሰብ ሆነ ህዝብ ውስጥ ይገኛሉና፣ መኖራቸው ምን ያህል የህዝብና የሐገር ጠንቅና ሸክም እንደሆኑ ለመመልከት

ወያኔን እንደ ምሳሌ መውሰድ በቂ ነው። ኢትዮጵያኖች ግፍን መፍራትና መሸሸ፣ ''ይሉኝታ (ሰው ምን ይለኝ)'' የሚለውንም ይትባህል የማጥበቃችንና የኢትዮጵያኖች የቆየ መለያችን መሆኑን ሳስብ ይህንን አሴታችንን ይህ ጉደኛው ወያኔ ምን ያህል እንደተፈታተነውና እየሸረሸረው እንደሆን ለመገንዘብ አይሳንም። ይሉኝታ ቢስ የሆነው ወያኔ ''**ዘረ ቢሶች በኢትዮጵያዊነት ሲነግዱ**'' ብሎ ሲያሽካካ፣ ''ዘር/ጎጥ'' የሚለውን ተውሶካ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ዘርቶ ለማብቀል የሚሞክር እሱው ራሱ መሆኑን እንኳ ለአፍታ ሊመለከት አለመቻሉ፣ ወያኔ ማለት ይሄ መሆኑን ገላጭ ነው። ይህ ጉደኛ ተምች በኢትዮጵያ ከተበተነ ጀምሮ እንደ ሥርዓት(ሲስተም) በሕዝብና በአገር ደረጃ ያደረሰውን የባህልና የሥነ ምግባር መዛባት በቀላሉ መገመት አይቻልም። አንድ ላይ ተባብረን ነቅለን ካልጣልነው ጦሰኛ ነውና!

ይህንን የደደቢት ተምች በኃይሉ (ገሞራው) ዲዲቲ ልርጨውና ልገላገል እስቲ፦

**ሌላውን ዓካሌን ሳትበክል መርዛ፣**
**ቆርጠኃት ጣልልኝ በነፍስ የለም ዋዛ።**

ከ'ቆርጠህት ጣልልኝ' የኃይሉ ገሞራው መጽሐፍ የተወሰደ

አመስግናለሁ ጋሼ ኃይሉ (ገሞራው)

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቸር ይግጠመን
ሜይ 15 / 2008